BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## Different meals

## የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች

*This is not a word-for-word transcript*

**ዘሩባቤል**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ሊያውቃቸው የሚገቡ የቋንቋ መሰረታዊያንን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation እንኳን በደህና መጡ። ዘሩባቤል እባላለሁ። በዚህ ክፍል ሰዎች ምን እንደሚመገቡ መጠየቅን ይማራሉ።
ሁለት ሰዎች ብዙ ጊዜ ስለሚመገቧቸው የምግብ ዓይነቶች ሲነጋገሩ ያዳምጡ።

***Phil***
*Hi Sian. What do you eat for breakfast?*

***Sian***
*I usually eat porridge for breakfast. What about you?*

***Phil***
*I always eat fruit.*

**ዘሩባቤል**
ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን።
የመጀመሪያው ተናጋሪ ሁለተኛዋን ተናጋሪ ቁርስ ‘breakfast’ ምን እንደበላች ነው የጠየቃት። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*What do you eat for breakfast?*

**ዘሩባቤል**
ሁለተኛዋ ተናጋሪ ‘usually’ አዘውትራ የምትመገበው ‘porridge’ ገንፎ መሆኑን መልሳለች። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*I usually eat porridge for breakfast.*

**ዘሩባቤል**
ከዚያ የመጀመሪያውን ተናጋሪ ተመሳሳይ ጥያቄ አቀረበችለት። አንድ ሰው የጠየቃችሁን ጥያቄ መልሳችሁ ለጠያቂው ማቅረብ ስትፈልጉ ‘What about you?’ አንተስ ወይንም አንችስ ማለት ትችላላችሁ። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*What about you?*


© British Broadcasting Corporation 2018

**ዘሩባቤል**
የመጀመሪያው ተናጋሪ 'always' ሁልጊዜ ለቁርስ 'fruit' ፍራፍሬ እንደሚበላ ተናግሯል።

*I always eat fruit.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤ ያሉትን ለማጣራት የተለያዩ ሰዎች ስለተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ሲነጋገሩ ያዳምጡ።
ሮብ 'lunch' ለምሳ 'fish stew' የዓሳ ወጥ ይበላል። ኒኮል ደግሞ 'chicken' ዶሮ እና 'rice' ሩዝ ትበላለች።

*Hi Rob. What do you eat for lunch?*

*I usually eat fish stew for lunch. How about you?*

*I usually eat chicken and rice.*

ሄዘር ለራት የበግ ስጋ 'lamb' ስትበላ ኒክ ደግሞ አትክልት 'vegetables' ይመገባል።

*Hi Heather. What do you eat for dinner?*

*I always eat lamb for dinner. What about you?*

*I usually eat vegetables.*

**ዘሩባቤል**
እሺ፤ አሁን ደግመን እንሞክረው። የእንግሊዝኛ አረፍተ ነገሮቹን ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ይሰማሉ።

*What do you eat for breakfast?*
*What do you eat for breakfast?*

*I usually eat porridge for breakfast.*
*I usually eat porridge for breakfast.*

*What about you?*
*What about you?*

*I always eat fruit.*
*I always eat fruit.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ! እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንደሚያስታውሱት እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።

*ለቁርስ ምን ትበያለሽ?*
*What do you eat for breakfast?*


© British Broadcasting Corporation 2018

*ቁርስ አዘውትሬ የምበላው ገንፎ ነው።*
*I usually eat porridge for breakfast.*

*አንተስ?*
*What about you?*

*እኔ ሁሌም ፍራፍሬ ነው የምበላው።*
*I always eat fruit.*

**ዘሩባቤል**
ግሩም! አሁን ምግብ ቤት ገብተው ምግብ በእንግሊዝኛ እንዴት ማዘዝ እንደሚችሉ ያውቃሉ። ለሲያን ምላሽ በመስጠትና የሚፈልጉትን በመናገር ይለማመዱ።

*What do you eat for breakfast?*
*I always eat fruit.*

**ዘሩባቤል**
አሁን መልስዎን ለማጣራት ሙሉውን ውይይት ያዳምጡ።

***Phil***
*Hi Sian. What do you eat for breakfast?*

***Sian***
*I usually eat porridge for breakfast. What about you?*

***Phil***
*I always eat fruit.*

**ዘሩባቤል**
በጣም ጥሩ፤! አሁን ሰለምግብ ሰዓት እና ዓይነቶች በእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር ችለዋል። የተማሩትን መለማመድ አይዘንጉ። ጓደኛ ይፈልጉና በእንግሊዝኛ ምግብ በማዘዝ ልምምድ ያድርጉ። ለተጨማሪ የዕለት ተዕለት እንግሊዝኛ በሚቀጥለው ዝግጅታችን ይጠብቁን።


© British Broadcasting Corporation 2018